## አቶ ዝናቡ ጣሰው 'Distinction between civil service and political service 'በሚል በፃፉት ገንቢ አስተያየት ላይ አቶ ግርማ ና መሰሎቻቸው ለሰጡት ትችት የተሰጠ ምላሽ

*በመጀመሪያ እኔ ሳላውቃችሁ ሙያየን ና የስራ ልምዴን አስመልክቶ ለህዝብ ከሞላ ጎደል ስላስተዋወቃችሁ ሳላመሰግናችሁ አላለፍም።*

*ይህም ሆኖ በቅርብ የሚደግፏችሁንና የምታጎበድዱላቸውን ከፅሀፊ ትህዛዝ አከሊሉ ተርታ ለማቀራረብ መሞከራችሁ የተለመደው ተክህኖ ስራችሁ ስለሆነ ህሊናየ የማይቀበለው ተግባር ና ከወዲሁ ሀርስ በርሳቸሁ ራሳችሁን ተራራ ላይ ቁብ ለማድረግ መሞክራችሁ ' እንቁራሪት በሬን አክላለሁ ብላ ፈንድታ አረፈች" የሚለው ትብህል እንዳይደርስባችሁ ያስፈራል።*

*እንደርስወ በስድብና በማስፈራራት ትምህርተ ተክኖየን አላጓድፍም። የእርስወ ትምህርት ግን በታወቀ አካዳሚክ ተቋም እውቅና እስኪቸረው ድረስ ለሚሉት ሁሉ ነወት ለማለት አይዳዳኝም::*

*ይህን አስተያየት በአማረኛ ልፅፍ የተገደድኩት የምኮራበት በመሆኑ: ምክር አዘል የሆነውን ቀድምት ፅሁፌን ከእግሊዝኛ ወደ ሚገባው መንገድ የሚተረጉምልወ ግለሰብ ሙያዊ ተክህኖ የለሌው ወይም በፅሁፊ ዕውነተኛነት በርግገው መሆኑን በመገንዘብ ና በዕርስወ ርካሽ ዳረንጎት ተገፍተው በአማረኛ ለተቼት ባልደረባው ጭምር በሚገባችሁ ዘያዊ ና ገላጭ በሆነ መልክ ሙያዊ ዕገዛና ምክሪን ጀባ ልላችሁ ገዶኝ ነው::*

*አቶ ግርማ ጥገኝነት አግኝተው በምኖሩበት እንግሊዝ ሀገር ስራ -ፈት ሁነው ሲቅበዘበዙ ያዋጣኛል ብለው ህዝብን አጋፍጠው ና ሸጠው ሀገር ቤት የተመለሱትን ግለሰቦች የማሞካሸቱን ትግባር ስራየ ብለው መያዝወ: በስራችሁ ና በሙያችሁ ያለገኛችሁትን ምኞተ ሙከሻ ለማገኝት ስትሉ በወድሞቻችን አስከሪን ለመነገድ ና ገመናችን በማሰረይ/በማሳየት/ ኪሳችሁን እንደመሰሎቻችሁ ለማድለብ መሞክራችሁ በታሪክ የሚያስጠይቃችሁ መሆኑን ከወዲሁ እንድትገነዘቡት እወዳለሁ ::*

## እንደገና የተወለደ ጀግና / A born again patriot/ ሰለሚለው

*ደግሜ ደጋግሜ እንዳስረገጥኩት ኢትዮጵያ በጀገኖች ልጆቿ እንጅ እንደእናነተ ባሉት ባንዳ የፈረንጅ አጎበዳጆች ነፃነቷን ታገኛለች ብሎ የሚያስብ ኢትዮጵያዊ እንደሌሌ ከወዲሁ እንድታውቁት እወዳለሁ::*

እራያ ና ቆቦ/ ፍሬ ፈርስኪ/ በሆነው ትችትው ወይም የቋንቋው ተክህኖ ክዶውት 'እንደገና የተወለድክ ጀግና" ነህ በሚል ያላበሱኝ ማዕረግ የሚገባኝ አገላለፅ ስለሆን በድጋሜ አመሰግንወታለሁ::

እንደ ጅግኖች ኢትዮጵያውያን ጦር ሜዳ ተሰልፌ እንደናንተ ካለው ሀገር ና አስከሬን ሻጭ ካሃዲውች ጋር ግብ ግብ የመግጠሙ የወደፊት ዓላማ እንዳለ ሆኖ እንደናንተ ግን ወገኔን ከባህዳን ጋር ዶልቸ ላደማው ና ላናቁረው አይዳዳኝም::

ለባዕድ አልንበረከክም ማለቱንና ወገኔን ተው በባንዳ ነፍስ ሺያጭ የእግዲህ ልጆች አትታለል ማለቱን አያቶቹ ያሰሩልኝ ማተብ ስለሆን አልፈታውም ::

ከልጅነቴ ጀምሮ ለሕዝብ ነፃነት ጦር ከስነጉት ጋር እንደናነተ ያለውን የሞስኮቭ ክትብ ቀይ ሽብር አፋፋሚውች በሚመስለኝ መልኩ ተዋግቻለሁ:: ከእናንተም ጋር ለመሰለፍ ያልዳዳኝ ውስጣችሁ ያልጠራና በግል ቂም የተሞላችሁ ጠባቦችና ምንደኞች ስለታጎሩባችሁ ነው:: እስታሊናዊ ምዕናብ ካለው ቡድን ጋር ለመሰራት በፍፁም እኛ አትዮጵያውያን አንሞክረውም:: ከሕዝብ የሚደበቅ እንደሌሌ ዕወቁ::

በባድሜ: በቡሬ ና በመሰሎቹ የግንባር ጦርነት ወቅት በግንባር ቀደምትነት ድጋፍ ከማሰባሰብ ጀምሮ እስከ ጦር ግንባር ወርዶ ለመፋለም ቃል ከመግባት ባሻገር ከጀግናው አትዮጰያዊ ሰራዊት ጎን እንደምንሰለፍ የሞራል አይዞነቱን የቸርን አትዮጵያዊ የኩሩ ሕዝብ ሀብራክ ክፋይ ነን እንጂ የፈረንጅ ኮቲ የምንከተል አየደለንም:: በዚህ ና በተመሳሳይ የሀገራችን የከፋ ዘመን ሀርስወ ና መሰሎችው የት ነበሩ ?

ከዘያም ጦርነቱ በተገባዳደ ማግስት ስለ ሀገሬ ተጨባጭ ሁኔታ ወደ እንግሊዝ ሃገር እንደ እርስወ ና መሰሎችው በስነ ምግባር ብሉሽነት በመባረር ሳይሆን ሃገሬ በምን መልክ መዋቀር አለባት: እንዴትስ ችግራችን በብሔረ ብሔረስብ 'አንድነትና ልዩነትን በመከባበር" /Unity respecting diversity/ በሚለው የሰላም አካሄድ ብትጓዝ የሚበጃት ስለመሆኑ ና ስለአለው የሀገራችን ሂደት ለሰላም ወዳዱ ህዝቤ ና ለሚመለከተው አካል በልበ ሙሉነት ያስረዳሁ ና በማስረዳት ላይ ያለሁ የምወዳትን ሀገሬን ሳልወድ ርቄ የምናፍቃት ና በሰው ሃገር መኖር የሚኮሰኩስ መሆኑን ያልዘነጋሁ ኩሩ የኢትዮጵያ አብራክ ክፋይ መሆኔን ልገልፅ እወዳለሁ።

ሀርስወ ና መሰሎችው በአንዳንድ ስብሰባወች የበሂር በሂረሰቦች መብት በፅንፈኞች ሲነካ: ሲደፈር ና ትግላቸው በንቀት ሲታይ ለማረም የማይዳዳችሁ ና የተወሰኑ ብሂሮችን በጥላቻ እንደመሰሎቻችሁ በጎሪጥ የሚታዮ ጠባብ የብሔርተኝነት ስሜት የተጠናወታቸሁ መሆኑን አስረግጨ እናገራለሁ:: ይህም እግዚሐብሔር ከፈቀደ በጥናት አስደግፌ ለማቀርብ እየተዘጋጀሁ ስለሆነ የመላው ኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ እሻለሁ:: ከዚህ ተግባራቸሁም እንዲትታቀቡ ውጭ ሀገር ለሚገኙ ድሕረ ገፆች በሚከተለው መልኩ አሰራጭቻለሁ:

You are not the mouthpiece of all Ethiopians; rather igniting hostility among our people. Your wording is vague and people couldn't understand it. Technology is booming, in spite of the fact that you are

living in the past. You must be realistic and push ahead to depict the real world in a very constrictive and lucid way. Your wording should be clear and sagacious. I am recommending you to go back home and rehearse the knowledge of approaching people in a very elegant and intellectual way.

*ይህን ተመርኩዞ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነዚህ ተኩላወች እና ለጥቅማቸው ካደሩ እንዲሁም በኢትዮጵያውያን ክቡር ገላ በስተጀርባ ከሚነግዱ አስመሳዮች መጠንቀቅ ያሻዋል እላለሁ::*

*አቶ ግርማ በሰው ሀገር ትልቅ ሆኖ ለመታየት ማረዮ በሀገር ቤት ያላገኙትን ሹመት መናፈቁ ና የማይገባችሁን የክብር አክሊል ከሩቅ ሀገር ሆኖ ለመድፋት ማለሙ ራስን ከማጣት ና ፈረንጆቹ /Identity Crises/ እንደሚሉት የተጠናወታቸሁ መሆኑን ያሳያል:: ብስነአዕምሮ ሳይንስ አገላለፅ አንድ ሕፃን ልጅ በህፃንነቱ የእናት ጡት ከተነፈገ ሲያደግ እጁን የመጥባት ልምድ እንደመያሳዬው /Fixation ይሉታል የስነ አዕምሮ ተመራማሪወች/ ያጋጠማቸሁ ይመስለኛል:: በጉልምስና ዘመናቸሁ ያጣችሁትን ለማግኘት መፏገር ትርፉ መላላጥ ነው:: መጀመሪየውኑ ስለ ንፁህ ኢትዮጵያዊነታቸሁ ካላቸው የሕዝባቸን ጥላቻዊ አገላለፅ ና በቅርብ ከሚያውቋቸው እንደምንረዳዉ እንዲሁም ነጭ አፍቅሮተ ተፅክኗቸሁ አጠራጣሪነቱንያመለክታል::*

## <u>*የዕውሸት አባዜ የተቆራኛቸሁ ስለመሆኑ*</u>

*የእግዚአብሔር ቃል በቅዱስ መፃሐፉ :*

> 'There fore each of you must put off falsehood
> and speak truthfully to his neighbor, for we are
> members of one group" Ephesians 4:25

> *'እውሸት ለመናገር አይሰላም ምላሴ ለእውነት እሞታለሁ*
> *አልሳሳም ለነፍሴ" ጥላሁን ገሰሰ*

> *' እዉነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር' ጥቅሰ ኢትዮጵያ*

*አቶ ግርማ በአቶ ዘነበ ጣሰው የተፃፈው ቃል የሀሰት ኩነና ነው ብለው ካሰቡ ለሀገሬ ለምወዳት አትዮጵያ በመቆጭት እውነቱን ይፋ አወጣሁ እንጅ እናንተን ለመወጀል አለመሆኑን መላው የሀገሬ ሕዝብ እንዲአውቀው በቅድመያ እፈልጋለሁ::*

*እኛ ከሀገር ተሰደን ስንወጣ በስልጣን ኮረቻ ፊጥ ከማለት በፊት አንድነታችን ና ህብረታችን ይበልጣል ብለን እንጂ ሹመቱን ና ስልጣኑን ተንፍገን አልነበረም ።*

*በሜይ 13ቱ በሎንደን ባዘጋጃችሁት ስብሰባ የታደሙ የስብሰባ ተሳታፊ አዛውንቶች: እንደናንተ በሀሰት ኪሳችውን ሊያሳብጡ ያልመጡ ኢትዮጵያውያንን እና ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ ብሔር ብሄረሰብ አባላት አይታዘቡንም በማለት በድፍረት እና*

በንቀት ቢትደሰኮሩም እኔ ግን ጋዜጣዊ ክዕኖተ ሙያየን ህዝየ ቃል እንደትቀበልኳችህ ማወቅ የተሳናችሁ አይመስለኝም::

ይሂን የአሜሪካው ጋዜጠኛ ና መላው ተሳታፊ ሰናይ ሰናዩን ቃላችሁን እየዋጡ በእንቅልፍ ና  ዲስኩራችሁ የሰለቻቸው በመሆኑ/ሰብሳቢው የተናገሩት ሰለሆነ/ ጀሮ ያልሰጡት ሆኖ ካልሆነ በስተቀር ሀቅነቱ አያጠራጥርም ሌላም የሚያስጠይቃቸው ጉደይ ሰላለ ወደፊት የሕዝብ ፍርድ ይጠብቃቸዋል::

‵አፍ ሲያመልጥ ና ራስ ሲመለጥ ‵ አይታወቅም ይላል የሀገሬ ሰው:: መጀመሪያ ታዳሚውን ማወቅና የጥላቻ መርህ የማይከተል ወዘ ልወጥ መኖሩን ማስተዋል ነበረባችሁ::ከሁሉም በላይ በታውቂ ኖሮ ዲስኩር ከማብዛት ለቤቱ መድረኩን ከፍታችሁ ሃሰብን ማሸራሸር ነበር  የስበሰባ አካሄድ ስርዓቱ: የስብስባ አካሄድ ስርዐቱንም ልትካኑ ይገባችዋል:: እንደዳኞችም: እንደዳኛም ይቃጣቸሁ ነበር ::ያገሬ ሰው ‵አወቅሽ አወቅሽ ሲሏት ምን አደረገች″ እነደሚባለው  በቀሰማችሁት ቁንፅል ዕውቀት ተመፃደቃችሁ ::

በዘህ አጋጣሚ በስብሰባው የተገኘሁት የሙያተኛ ዳኞችን ገለፃ ለመስማት ነበር እንጂ የናንተን ጉራ አዘል  ዲሰኩር ከዚህ በፊትም ‵የማያድግ ጥጃ ከገመዱ ያስታውቃል″ እንዲሉ ተሳትፌም ስለማላወቅ  ደግፊአችሁ አልነበረም::

ሙያ አዘል ጥያቄ በመቅረቡ ከመድረኩ: ከተሳታፊወች: እንደሁም  ከአሜሪካ ድምፅ ቃል አቀባይ ለለተቸረኝ  አድናቆት በኢትዮጵያ ህዝብ ስም ምስጋናየን ላቀርብ እወዳለሁ ::

## ሊታወቅ የሚገባው

1 - ከሁሉ በፊት የፃፍኩት ገንቢ ሃሳብ በራሴ የፃሃፊነት ሙያዊ ተክህኖ ተከተበ እንጂ ሌላ ተደራቢ ሃይል እንደሌለለው ይህነንም ችሎታየን: ርትዕ የሆነውን ልሳኔን ና ብሩህ ሀስተያየቴን እራሳችሁም ከመድረኩ በማድነቅ የገለፃችሁት መሆኑን ።

2 - የምትፋሯቸው ና የማትወዱቸው ቡድኖች ካሉ እንደልማዳችሁ ከነሱ ጋር መነታረክ የምትችሉ መሆኑን።

3 - ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የወገንኩ አለመሆኔን።

4 - የምኖረው በነፃ ሀገር ስለሆነ ስለማውቀው የመፃፍ :የመተቸትና ብሩህ ሃሳብ የማቅረብ መብት ስላለኝ መብቴን በማስፈራራት መንፈግ የማትችሉ መሆኑን።

5- ያደኩ :የነቃሁ: ልምድ ያለኝ ባለሙያ ና በሙያየ ሰርቼ ሀገሬንና ወገኖቸን እያገለገልኩ ና በግል ተሰጥኦየ የረካሁ ና በመርካት ላይ የምገኝ ‵ላም አለኝ በሰማይ″ የሚል ራህይ የሌለኝ መሆኑን ።

# ተራ አሉባልታ ከማናፈስ የስልጡን ሀገሩን ካባ ተላብሳችሁ ለአቀርብኳቸው ለሚከተሉት ጥያቄውች መልሳችሁን ብትቸረኝ :

ሀ) የስልጣኔ ምልክት መስሏችሁ የፈረንጆችን ጥቅስ በየመድረኩ ከማነብነብ ና የአንዳንድ ሰወችን የውሸት ባዘቶ በየ ድህረ ገፁ ና በየስብሰባው ከመደረት የሌሎች ጀግኖችን ገድለ ውሎ ብትዘግቡ የተሻለ አይሆንም ውይ ?

ለ) የአንዳንድ ግለሰቦች ወደ ሀገር ቤት መግባት እንደ አቡነ ጳወሎስ መስዋት በመሆን ሰማእትነት ለመቀበል ከሆነ ብታሳውቁን ካልሆነ ግን በሰላም መኖሩ ከአለፈው ፀረ-መንግስት አቋማቸው አንፃር ሲታይ እንዴት እንደቀለላቸው ብታስረዱን ?

ሐ ) በቅርብ በተመለሱ: በተለይ በሎንዶን ሆናችሁ የሲቪክ ማህበራት ተወካይ ነን በምትሉት ና በአቶ ልደቱ መካከል ያለው ትስስር ክርና መርፌ መሆን ለሀገራችን የተቃዋሚውች እንቅስቃሴ ብሩህ ተስፋ ከፋች ከሆነ ብትዘረዝሩልን እንዲሁም ግኑኝነቱ የሚያሳስብ አይመስላችሁም ወይ ?

መ) በስሜት ይሁን በድፍረት ዳኞችንና ግለሰቦችን በየመድረኩ እርስዎ በማያውቁት ገብተው እንደሚፈተፍቱት አቶ ዘነበን የኢ. ሕ.አ.ዲ. ግ. አፈ ቀላጤ እንዳሉት ሁሉ በድህረ ገፆችም ጭምር አልኮነናችሁንም ወይ ? ይሄ አይነቱ አካሄድ ያዋጣል ወይ ?

ሠ) ለተግበራችሁ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ሀገር ቤት ገባን ያሉትን አካቶ የተለገሳችሁ የገንዘብ ሆነ የቁሳቁስ ድጋፍ ካለ እናውቅ ዘንድ ቢገለፅልን?

ረ) ከላይ የተመለከተው ሞቅ ያለ የገንዘብ ድጋፍ በአግባቡ ተግባር ላይ ዉሏል ይላሉ ወይ ? የኦዲት ሪፖርት ለሰፊው መምህራን ሆነ ለሕዝብ ያቀረባችሁበት አጋጣሚ አለ ወይ ?

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከናንተና ከኔ የበለጠ ውስጠ ሚስጥሩን ስለሚያውቅ ህዝብን በማታውቁት ጉዳይ እንደ እርጎ ዝንብ እየገባችሁ ከማጋጨት ና ከማናቆር ያለውን ያሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ የሚያውቀውን ብታማክሩ ና ልምድ ብትቀምሱ የተሻለ መሆኑን ብታገናዝቡ። ይህ ካልሆነ ግን ከመድረኩ ገለል ብትሉ የተሻለ ይመስለኛል :: አስራ አምስት ዓመት ከትግሉ መድረክ ርቆ ናተኝቶ ከርሞ አሁን መቧረቁ ሌላ ስለሚያስመስል በሕዝብ ሳትተፉ ይቅርታ ጠይቃችሁ ወደ ሕዝብ ጉያ መግባቱ የሚሻላችሁ መሆኑን ሙያየ በስጠኝ ልምድ ና በእግዚሐብሔር ስም አሳስባችዋለሁ::

# ማሳሰቢያ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ

*እውሸት የሚናገሩ አይበጁንመና እናጋልጣቸው።
*በኢትዮጵያን ስም ፡ አስከሬንና ገመና መነገዱ ይቁም።
* በሀገራችን አንኩራ።
*ስብሰባ ከተሳተፍን ሃሳባችን የማንሸራሸር በህል እናዳብር።
*ለሀገራችን ጉዳይ የጠባብነት አባዜ ሳያጠቃን በንቁ እንሳተፍ።
*በስብሰባ የበይ ተመልካች ለመሆን በቻ አንታደም።

`ዉሃ ና ንጋት እያደር ይጠራል" እንዲሉ
ስንዴው ከዕንክርዳዱ እየተለየ መጥቷልና ሁሉንም ለማየት እግዚሐብሔር ያብቃን::

`ኢትዮጵያ ታበፅህ እዳዊሀ ሀበ እግዚሐብሔር"
`ኢትዮጵያ እጆቿን ተሎ ወደ እግዚሐብሔር ታነሳለች"

መዝሙር 68: 31

አሜን::

ዘነበ ጣሰው ::